በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
በትራንስፖርት ሚኒስቴር
የማሪታይም ጉዳይ ባለስልጣን
The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Transport
Maritime Affairs Authority

ቁጥር No. ሃ 70/097/462/04/06
ቀን Date 18/04/ ፳፻06
አዲስ አበባ-ኢትዮጵያ
Addis Ababa, Ethiopia

ለኢትዮጵያ ባሕር ትራንስፖርትና ሎጀስቲክስ አገልግሎት ድርጅት፣

ለዕቃ አስተላላፊዎች፣

ለኢትዮጵያ ፍሬት ፎርዋርደርና ሺፒንግ ኤጀንት አሶስየሽን፣

አዲስ አበባ

ጉዳዩ፡- የኦፕሬሽን መረጃን አዲስ በተዘጋጀ ሶፍትዌር (Software) መላክን አስመልክቶ የወጣ የአሠራር ሥርዓት፤

የትራንዚት ጊዜና ወጪን የተመለከተና የተደራጀ ብሄራዊ የአገሪቱ የሎጅስቲክስ መረጃ የአገሪቷን ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ከማረጋገጥ ባሻገር ለአገልግሎት ሰጪና ተቀባይ እንዲሁም ለሃገር ቁልፍ ሚና እንዳለው ይታመናል፡፡ የማሪታይም ጉዳይ ባለስልጣን በተቋቋመበት አዋጅ ቁጥር 549/1999 ላይ ከተሰጡት ተግባራትና ኃላፊነቶች ውስጥ አንዱና ዋነኛው የገቢ እና የወጪ ዕቃዎች የትራንዚት ጊዜና ወጪን ኢኮኖሚያዊ አዋጭነት ማረጋገጥ ነው፡፡ ባለስልጣን መ/ቤቱ ይህንኑ ኃላፊነቱን በአግባቡ ለመወጣት ዘርፈ ብዙ ጥረቶች እያደረገ የሚገኝ ሲሆን ከነዚህ መካከል የገቢ ከፍተኛ ጭነት አመጣጥን ፣ የወጪ ደረቅ ዕቃዎች ትራንዚት ትራንስፖርት ሥርዓት እና የገቢ ዕቃዎችን የትራንዚት ትራንስፖርት ሥርዓት መመሪያዎችን በትራንስፖርት ሚኒስቴር አማካኝነት በማውጣት ከመጋቢት 15/2005 ዓ.ም ጀምሮ ሥራ ላይ እንዲውሉ አድርጓል፡፡

ከላይ በተጠቀሱት መመሪያዎች የአገሪቱ የገቢና ወጪ ዕቃዎችን የተመለከተ አጠቃላይ መረጃ የሚሰበሰብበትን ሥርዓት ከመዘርጋት አኳያ በዕቃ አስተላላፊነት የሥራ ዘርፍ የተሰማሩ ድርጅቶች ሊኖራቸው ስለሚገባ ድርሻ በተሰጣቸው ተግባር እና ኃላፊነት ውስጥ ከመገለጹም በላይ መመሪያዎቹን ለማስፈፀም በተዘጋጁት ስንታዳርዶች ውስጥም ተገቢው ሽፋን

የስልክ ቁጥር Telephones 0115 50 36 38 0115 50 36 83
የፖ.ሣ.ቁ P.O.Box 1861
ፋክስ FAX 0115 50 39 60

መልስ በሚፅፉልን ጊዜ የእኛን ደብዳቤ ቁጥርና ቀን ይጥቀሱ
IN REPLAYING PLEASE QUOTE OUR REFERNCE NUMBER & DATE

ተሰጥቶታል፡፡ ከነዚህም ተግባራትና ኃላፊነቶች መካከል ባለስልጣን መ/ቤቱ በሚዘረጋውና በየጊዜው ወቅታዊ በሚያደርገው የመረጃ ልውውጥ ሥርዓት መሠረት የሚያከናውኑትን ኦፕሬሽን ለባለሥልጣን መ/ቤቱ ፀየጊዜው ማሳወቅን ያካትታል፡፡

በዕቃ አስተላላፊነት ሥራ ላይ የተሰማሩ ድርጅቶችም ቀደም ሲል ብቃትን ከመከታተል ጋር ተያይዞ በየወሩ የሚያቀርቡት የሥራ ክንውን ሪፖርት እንደተጠበቀ ሆኖ የሚያከናወኑትን የኦፕሬሽን መረጃዎችን በተዘጋጀላቸው ስታንዳርድ ቅጽ መሠረት በየዕለቱ በኢ-ሜይል አማካኝነት ለባለስልጣን መ/ቤቱ ሲልኩ ቆይተዋል፡፡

ይሁንና በኢ-ሜይል በየቀኑ ከተለያዩ ዕቃ አስተላላፊ ድርጅቶች የሚመጣበት የመረጃ ቅብብሎሽ ሥርዓት ለመረጃ ላኪዉና ተቀባዩ ከፍተኛ የሥራ ጫና መፍጠሩ በዕቃ አስተላላፊና እንዲሁም በባለሥልጣን መ/ቤቱ በተደረገ ግምገማ በመረጋገጡ የተጠቀሰዉ ችግር መፈታት እንዳለበት ታምኖበታል፡፡ በመሆኑም የገቢና ወጪ ዕቃዎችን ኦፕሬሽን በተመለከተ ሙሉ መረጃን ከዕቃ አስተላላፊዎች ተቀብሎ እና አጠናቅሮ ለባለሥልጣን መ/ቤቱ የሚያሳውቅ እንዲሁም የመረጃ ቅብብሎሹን የሚያዘምን ሶፍትዌር (software) ተዘጋጅቷል፡፡

ሶፍትዌሩ (software) በሰው ተዘጋጅቶ በኢ-ሜል ይላክ የነበረውን አድካሚውን የመረጃ ልውውጥ ሥራ ሙሉ ለሙሉ የሚያስቀር እና ዕቃ አሰተላላፊ ድርጅቶች የተጣለባቸውን መረጃ የመላክ ኃላፊነት ያለምንም ተጨማሪ ድካምና የሰው ኃይል በአግባቡ ለባለሥልጣን መ/ቤቱ የሚልኩበት፤ ባለሥልጣን መ/ቤቱም የገቢ እና የወጪ ዕቃዎች ኦፕሬሽንን በተመለከተ የተሟላ መረጃ በአግባቡና በየጊዜው የሚያገኝበትን ሁኔታ ይፈጥራል ተብሎ የታመነ ሲሆን ይህንንም በተመረጡ የዕቃ አስተላላፊዎች እና በባለስልጣን መ/ቤቱ በኩል በሶፍትዌሩ ላይ በተደረገዉ የሙከራ የመረጃ ልውውጥ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

በመሆኑም ማንኛዉም በዕቃ ማስተላለፍ የአገልግሎት ዘርፍ ለመሠማራት ከባለሥልጣን መ/ቤቱ የብቃት ማረጋገጫ አግኝተዉ የሥራ ፈቃድ በማውጣት ሥራቸዉን እያከናወኑ የሚገኙ ድርጅቶች ይህን ሶፍትዌር በመጠቀም ወቅታዊና ትክክለኛ መረጃ በተገቢው ጊዜ ለባለሥልጣን መ/ቤቱ መላክ እንዳለበት ስለታመነበት ይህ የአሠራር ሥርዓት ተዘርግቷል፡፡ ለአሠራር አመቺ ይሆን ዘንድም ሶፍትዌሩ በኢትዮጵያ ፍሬት ፎርዋርደርስ ኤንድ ሺፒንግ ኤጀንት አሶስየሽን በኩል ለሁሉም ዕቃ አስተላላፊዎች እንዲደርስ ተወስኗል፡፡

ይህ የአሠራር ሥርዓት አስገዳጅ ሲሆን ማንኛዉም ዕቃ አስተላላፊ ከጥር 1/2006 ዓ.ም ጀምሮ ሶፍትዌሩን እና የአጠቃቀሙን ሥልጠና በሚዘጋጀው መርሃ- ግብር መሠረት ከአሶሴሽኑ በማግኘት ወደ ትግበራ እንዲገባ እየገለጽን ይህንን በማይተገብር ዕቃ አስተላላፊ ድርጅት ላይ ባለሥልጣን መ/ቤቱ አስፈላጊዉን አስተዳደራዊ እርምጃ እንደሚወስድ እናስታዉቃለን ።

Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Transport Maritime Affairs Authority

ከሠላምታ ጋር

መኮንን አበራ
ዋና ዳይሬክተር

ግልባጭ፡-

- ለትራንስፖርት ሚኒስቴር
  አዲስ አበባ